# ሒሳብ

## የመምህር መምሪያ መጽሐፍ

## 3ኛ ክፍል


አዘጋጆች፡-

አብዩ አንተነህ

ይብሬ አህመድ

ፍቅረ አሰፋ

ገምጋሚዎች

ሙስጠፋ ከድር

ሮዳስ ድሪባ

ገስጥ አሰፋ

ሌይ አውት እና ኢሉስተሬሽን ዲዛይን፡-

ግርማ ዳርጌ

ኃይለጊዮርጊስ ተመስገን

አስተባባሪ

ጌታቸው ታለማ አጥናፉ



አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

© 2015 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱትን ጥቅሶችና ሥዕሎች በምንጭነት
የተጠቀመባቸውን ሁሉ እናመሰግናለን፡፡

## ምስጋና

ይህን የትምህርት መጽሐፍ ከዝግጅት ጀምሮ በውጤት እንዲጠናቀቅ፣ የካበተ ልምዳቸውን በማካፈል፣ በፓናል ውይይት ሃሳብ በማፍለቅና በማቅረብ፣ በከተማችን በሚያስተምሩ መምህራን እንዲዘጋጅ በማድረግ፣ አስፈላጊውን በጀት በማስፈቀድ እንዲሁም በጥብቅ ዲስፕሊን እንዲመራ በማድረጋቸው ላደረጉት ከፍተኛ ድጋፍ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ዘላለም ሙላቱ የላቀ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

ለስራችን መሳካት ሁልጊዜ አብረውን በመሆን ፣ በሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት፣ የአፈጻጸም ሂደቱን በመከታተል፣ በመገምገም እንዲሁም የዝግጅቱ ስራ ቁልፍ ስራ መሆኑን ተረድተው ትኩረት በመስጠት ከጎናችን ለነበሩ የትምህርት ቢሮ የማኔጅመንት አባላት የስርዓተ ትምህርት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አድማሱ ደቻሳ፣ የትምህርት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳኛው ገብሩ፣ የመምህራን ልማት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሳምሶን መለሰ፣ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አማካሪ ወ/ሮ አበበች ነጋሽ፣ የትምህርት ቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ሲሳይ እንዳለ፣ የቴክኒክ አማካሪ አቶ ደስታ መርሻ ላበረከቱት አስተዋጽኦ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

በመጨረሻም መጽሐፉ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን ለስራው ልዩ ትኩረት በመስጠት አዘጋጅ መምህራንን ስለላካችሁልንና የሞራል ድጋፍ ስላደረጋችሁም ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## 1. እስከ 10000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች እና ቅደም ተከተላቸው

### መግቢያ

የዚህ ምዕራፍ ትኩረት እስከ 10000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች እና ቅደም ተከተላቸው መገንዘብ ሲሆን ይህንን አላማ ከግብ ለማድረስ አራት ንዑስ ርዕሶችን ይሸፍናል፡፡እነሱም 1000 ሙሉ ቁጥሮችን ክለሳ፣እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ማስላት፣እስከ 10000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች የ100 እና 1000 ብዜቶች ፣እስከ 10000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች እና እስከ 10000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደር ይማራሉ፡፡

ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ማስተማር ውጤቶች

- የሙሉ ቁጥሮች የቤት ዋጋ ይረዳሉ::
- እስከ 10000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ማወዳደር እና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ይረዳሉ::
- እስከ 10000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በእለት ተእለት ህይወታቸው ውስጥ ይተገብራሉ፡፡

ምዕራፍን ለማስተማር በዋናነት የሚያስፈልጉ የትምህርት መረጃ መሳሪያዎች

የመደመር ፣ የመቀነስ እና የማባዛት ምልክቶች የተፃፉባቸው ካርዶች፣ የማባዛት ሰንጠረዦች፣ የማባዛት የቁጥር ቤት ሰንጥረዦች ፣ ተደራራቢ የመደመር ሳጥኖች እንዲሁም ፎቶዎችን እና ስዕሎች ይገኙበታል፡፡

## 1.1 በ100 እና በ1000 መቁጠር

የተመደበው ክ/ጊዜ፡2

### 1.1.1 ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የብቃት መስኮች

በ100 እና በ1000 መቁጠር

### 1.1.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የመማር ማስተማር ዘዴዎች እና ተግባራት

- እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ተግባራዊ ጥቅማቸውን በመግለፅ ትምህርቱን መጀመር

- ተማሪዎ ችን በቡድን በመመደብ የአቆጣጠር ጽንሰ ሃሳብ እንዲያዳብሩ ማድረግ፡፡
- የመቁጠሪያ ቁጥሮች እና የሙሉ ቁጥሮችን ልዩነት እንዲረዱ ማድረግ

### 1.1.3 የምዘና ስልቶች እና ዝርዝር ተግባራት

- እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች የ100 እና የ1000 ብዜቶችን በቃላቸው እንዲናገሩ መጠየቅ
- ከተግባር ሀ የተወሰኑትን የግል ፣ የቡድን ስራ፣እንዲሁም ተጨማሪ ጥያቄዎችን የቤት ስራ በመስጠት ተማሪዎችን እስከ 1000 የሚደርሱ ቁጥሮችን እንዲያስታውሱ ማድረግ
- እስከ 1000 ያሉ ቁጥሮችን በትክክል እንዲያነቡ እና መፃፍ እንዲችሉ ማድረግ
- የተለያዩ ተግባራት እና መልመጃዎችን ማሰራት እና ስህተታቸውን እንዲያርሙ ማሳየት፣ማበረታታት እና ለሚቀጥለው ርዕስ ማዘጋጀት፡፡
- እስከ 1000 ያሉ የ1000ብዜቶችን በቃላቸው እንዲናገሩ መጠየቅ፡፡
- ተጨማሪ ጥያቄዎችን መጠየቅ በዝግታለሚረዱ ተማሪዎች ጥያቄዎች

ሀ.5490 ሺዎች፣ ስንት መቶዎች እና ስንት አስሮች እንዳሉ ፃፉ::

ለ.2400 የ100 ወይም የ1000 ብዜት መሆኑን ለዩ ::

**በፍጥነት ለሚረዱ ጥያቄዎች**

ሀ.5693 በአንድ ቤት፣ በአስር ቤት ፣ በመቶ ቤት እንዲሁም በሺ ቤት በመተንተን ፃፉ::

### 1.1.4 መልሶች

**ተግባር ሀ**

1.7 00

2.4 ሺዎች እና 5 መቶዎች

3.ሀ 3600 ሶስት ሺ ስድስት መቶ

ለ 4500 አራት ሺ አምስት መቶ

መልመጃ ሀ

1. ሀ.5621 5 ሺዎች፣6 መቶዎች፣2 አስሮች እና 1 አንድ
   ለ.9082 9 ሺዎች፣0 መቶዎች፣8 አስሮች እና 2 አንዶች
   ሐ.6640 6ሺዎች፣6 መቶዎች፣4 አስሮች እና 0 አንድ
2. ሀ 8449
   ለ 1682
   ሐ 5208
3. ሀ 3203
   ለ 5433

## 1.2 እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች የቤት ዋጋ

### የተመደበው ክ/ጊዜ፡7

### 1.2.1 ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች

- እስከ 10000 ያሉ ቁጥሮችን የቤት ዋጋ መለየት

### 1.2.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የመማር ማስተማር ዘዴዎች እና ተግባራት

- ምሳሌ ሀ በክፍል ሰርተው ምሳሌ ለ ደግሞ በግል እንዲሰሩ እና መልሳቸውን እንዲያረጋግጡ ማድረግ።
- እስከ 1000 የሚደርሱ ሙሉ ቁጥሮችን ማንበብ እና በፃፍ ከቻሉ ስንት አንድ፣ ስንትመቶ ፣ ስንት ሺዎች እና ስንት አስሮች እንዳሉ እንዲረዱ ማድረግ።
- በመቀጠልም የሺ ቤት ሆሄ፣ የመቶ ቤት ሆሄ፣የአስር ቤት ሆሄ እና የአንድ ቤት ሆሄያትን የሚያሳዩትን እንዲለዩ ማድረግ

### 1.2.3 የምዘና ስልቶች እና ዝርዝር ተግባራት

- እስከ 10000 ባሉ ሙሉ ቁጥሮችን የቤት ዋጋ እንዲለዩ በተለያየ ካርዶች ቁጥሮችን በመፃፍ የአንድቤት፣የመቶ ቤት፣ የሺቤት በመለየት እንዲናገሩ እና እንዲፅፉ ማድረግ
- ከመልመጃዎች የተወሰኑትን የግል ፣ የቡድን እንዲሁም የቤት ስራ በመስጠት የተለያዩ ተግባራት እና መልመጃዎችን ማሰራት
- መልመጃዎቹን ከሰሩ በኋላ ተጨማሪ ጥያቄዎችን የክፍል ስራ በመስጠት ተማሪዎቹን ይመዝኑ፡፡

- ተጨማሪ ጥያቄዎችን መጠየቅ

  በዝግታ ለሚረዱ ተማሪዎች ጥያቄዎች

  ሀ. 3400 የሺ ቤት ሆሄውን ፃፉ?

  በፍጥነት ለሚረዱ ተማሪዎች ጥያቄዎች

  ሀ. 45093 ከዚህ ቁጥር 4 የስንት ቤት እንደሆነች ፃፉ?

### 1.2.4 መልሶች

መልመጃ ሀ

1.

| | የአስር ሺ ቤት | የአንድ ሺ ቤት | የመቶ ቤት | የአስር ቤት | የአንድ ቤት |
|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | 3 | 4 | 5 | 1 | 2 |
| ለ | | 3 | 0 | 9 | 8 |
| ሐ | | | 1 | 2 | 9 |
| መ | | 2 | 3 | 0 | 5 |

2. ሀ 2513

   ለ 3503

   ሐ 9981

   መ 1816

3. ሀ. 3526 ሶስት ሺ አምስት መቶ ስድስት

   ለ. 908 ዘጠኝ መቶ ስምንት

   ሐ. 9984 ዘጠኝ ሺ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ አራት

4. 1. መ

   2. ሐ

   3. ሠ

   4. ለ

   5. ሀ 6. ረ

## 1.3 እስከ 10000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደር
## የተመደበው ክ/ጊዜ፡4

### 1.3.1 ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች

- እስከ 10000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደር

### 1.3.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ውይም በአማራጭነት የመማር ማስተማር ዘዴዎች እና ተግባራት

- እስከ 10000 ያሉ የ100 እና የ1000 ብዜቶችን እንዲፈልጉ ተማሪዎችን በቡድን ማደራጀት ፣እርስ በርስ እንዲደጋገፉ መርዳት
- ምሳሌ ሀ በክፍል ሰርተው መልሳቸውን እንዲያረጋግጡ ማድረግ እንዲሁም ምሳሌ ለ እና ምሳሌ ሐን እንዲገነዘቡ ማድረግ

### 1.3.3 የምዘና ስልቶች እና ዝርዝር ተግባራት

- የተለያዩ ሙሉ ቁጥሮችን እንዲያወዳድሩ መጠየቅ
- እስከ 10000 ባሉ ሙሉቁጥሮች ተግባራዊ ፕሮብለሞችን እንዲሰሩ መጠየቅ
- ከመልመጃዎች የተወሰኑትን የግል ፣ የቡድን እንዲሁም የቤት ስራ በመስጠጥ ተማሪዎችን እስከ 10000 የሚደርሱ የ100 እና የ1000 ብዜቶችን እንዲለዩ በቃል እንዲሁም በፅሁፍ እንዲለዩ ማድረግ
- መልመጃዎቹን ከሰሩ በኋላ ተጨማሪ ጥያቄዎችን የክፍል ስራ በመስጠት ተማሪዎቹን ይመዝኑ፡፡
- ተጨማሪ ጥያቄዎችን መጠየቅ

በዝግታ ለሚረዱ ተማሪዎች ጥያቄዎች

ሀ. 700 እና 890 አወዳድሩ

ለ. 8000 እና 1250 አወዳድሩ

በፍጥነት ለሚረዱ ተማሪዎች ጥያቄዎች

ሀ. 3266 እና 3278ን አወዳድሩ

### 1.3.4 መልሶች

**መልመጃ ሀ**

1. ሀ. 567< 5677 ለ. 989 >99

ሐ.3888 > 880 መ. 760 < 7600

ሠ.4562 =4562 ረ. 8970 >999

**ተግባር ሀ**

ሀ. 20 < 30 ለ. 36 >16 ሐ .57< 95

መ. 28>25 ሠ. 72 < 74

**መልመጃ ለ**

1. ሀ.456 <3567 ለ. 2908>2899

ሐ. 4567 <4589 መ.5009<5109

2. ሀ.486 < 691 ለ. 542> 534

ሐ. 891 < 896 መ.4879 >4859

## 1.4 እስከ 10000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ

**የተመደበው ክ/ጊዜ፡4**

### 1.4.1 ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር የብቃቶች

- እስከ 10000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ

### 1.4.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ውይም በአማራጭነት የመማር ማስተማር ዘዴዎች እና ተግባራት

- ተማሪዎች ጥያቄ እንዲጠይቁ ፣ሃሳባቸውን እንዲያንፀባርቁ፣ እርስ በርስ እንዲነጋገሩ መርዳት
- እስከ 10000 የሚደርሱ ሙሉ ቁጥሮችን የቤት ዋጋቸውን እንዲለዩ
- ምሳሌዎችን በክፍል ሰርተው መልሳቸውን እንዲያረጋግጡ ማድረግ እና የማጠቃለያ ሃሳብ እንዲሰጡ ማገዝ

### 1.4.3 የምዘና ስልቶች እና ዝርዝር ተግባራት

- እስከ 10000 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች ተግባራዊ ፕሮብሌሞችን እንዲሰሩ መጠየቅ
- ከመልመጃዎች የተወሰኑትን የግል ፣ የቡድን እንዲሁም የቤት ስራ በመስጠት ተማሪዎችን እስከ 10000 የሚደርሱ ሙሉ ቁጥሮችን የቤት ዋጋ እንዲለዩ መጠየቅ እንዲሁም ቁጥሮችን በቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡ መጠየቅ
- መልመጃዎቹን ከሰሩ በኋላ ተጨማሪ ጥያቄዎችን የክፍል ስራ በመስጠት ተማሪዎቹን ይመዝኑ፡፡
- ቁጥሮችን ተንትነው የቢት ዋጋቸውን ማሳየት
- ተጨማሪ ጥያቄዎችን መጠየቅ

በዝግታ ለሚረዱ ተማሪዎች ጥያቄዎች

ሀ. የ687፣450፣12፣3400 እና 8900 ከትንሽ ወደ ትልቅ አስቀምጡ::

በፍጥነት ለሚረዱ ተማሪዎች ጥያቄዎች

ሀ. 2343፣2345፣2348፣2340፣2088 እና 2190 ከትንሽ ወደ ትልቅ እንዲሁም ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደ ም ተከተልአስቀምጡ::

### 1.4.4 መልሶች

ተግባር ሀ

1. ሀ.345፣1234፣5677 እና 6578

   ለ.89፣1002፣2345፣1400 እና 9087

2. ሀ.9008፣8909፣4459፣3421እና 78

   ለ.25554፣4255፣4250፣980 እና 890

መልመጃ ሀ

1. ሀ. 491፣ 521 ፣ 591 ፣ 831

   ለ. 28፣ 832፣3598፣ 7582

   ሐ. 1009፣ 2301፣ 5988፣6548

2. ሀ. 1986፣ 487፣ 425 ፣ 389፣ 345

ለ. 8000፣1000፣999፣125

3. ሀ. ሃያት

ለ .አቤል

## 1.5 እስከ 10000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ10፣በ100 እና በ1000 ቤት ማጠጋጋት <u>የተመደበው ክ/ጊዜ፡6</u>

### 1.5.1 ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች

እስከ 10000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ10፣በ100 እና በ1000 ቤት ማጠጋጋት

### 1.5.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ውይም በአማራጭነት የመማር ማስተማር ዘዴዎች እና ተግባራት

- በቡድን በቡድን ሆነው በአካባቢያቸው የሚገኙ ነገሮችን መቁጠር እና እንዲያወዳድሩ ማድረግ
- ምሳሌዎችን እንዲረዱ እና ሃሳባቸውን እንዲያንፀባርቁ መርዳት፣ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው ቁመታቸውን እንዲያወዳድሩ ማድረግ
- እስከ 10000 ያሉ ሙሉ የ10 ቤት ፣የ100 ቤት እና የ1000 ቤት የአቃራብ ዋጋ እንዲፈልጉ ማድረግ
- ምሳሌዎችን በማየት የአቅራብ ዋጋ እንዲረዱ ማድረግ

### 1.5.3 የምዘና ስልቶች እና ዝርዝር ተግባራት

- ምልከታ ፣የወረቀት ሙከራዎች መስጠት
- የተማሪዎች የመማር ዉጤት እንዲሻሻል ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ መስጠት
- መልመጃዎቹን ከሰሩ በኋላ ተጨማሪ ጥያቄዎችን የክፍል ስራ በመስጠት ተማሪዎቹን ይመዝኑ፡፡
- ተጨማሪ ጥያቄዎችን መጠየቅ

በዝግታ ለሚረዱ ተማሪዎች ጥያቄዎች

ሀ.435 እና 479 የ10 ቤት አቅራብ ዋጋ ፈልጉ?

ለ.4360ን የ100 አቅራብ ዋጋ ፈልጉ?

በፍጥነት ለሚረዱ ተማሪዎች ጥያቄዎች

ሀ. ሺ ቤት አቅራብ ዋጋቸው 6000 የሚሆኑ ቁጥሮችን ቢያንስ ሶስት ቁጥሮችን ፃፉ?

ለ. የመቶ ቤት አቅራብ ዋጋቸው 4600 የሚሆኑ ቁጥሮችን ቢያንስ ሶስት ቁጥሮችን ፃፍ?

### 1.5.4 መልሶች

**ተግባር ሀ**

1. ሀ.30

   ለ.700

   ሐ.4000

**መልመጃ ሀ**

| ቁጥር | በ10 ቤት ሲጠጋ | በ100 ቤት ሲጠጋ | በ1000 ቤት ሲጠጋ |
|---|---|---|---|
| 6789 | 6790 | 6800 | 7000 |
| 4327 | 4330 | 4300 | 4000 |
| 2149 | 2150 | 2100 | 2000 |

## ማጠቃለያ መልመጃ

ሀ.

1. ሐ
2. ለ
3. ሐ
4. ሀ

ለ. የሚከተሉት ባዶ ቦታዎች <፣ > ወይም = በመጠቀም ሙሉ።

5. 412>7098
6. 2389>2379
7. 1948<1942
8. የሺ ቤት 6፣7 የመቶ ቤት፣5 የአስር ቤት እና 9 የአስድ ቤት
9. 452፣987፣4512 እና 4562
10. 1120፣1099፣1068፣1062 እና890
11. ሀ.5687= 5 ሺዎች + 6 መቶዎች+ 8 አስሮች+7 አንዶች

    ለ.4098=4 ሺዎች+0 መቶዎች+9 አስሮች+8 አንዶች

12.

| | የሺ ቤት | የ100 ቤት | የ10 ቤት |
|---|---|---|---|
| 2964 | 3000 | 3000 | 2960 |
| 3498 | 3000 | 3500 | 3500 |
| 9025 | 9000 | 9000 | 9030 |

# ምዕራፍ ሁለት

## እስከ 10000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር እና መቀነስ መግቢያ

የዚህ ምዕራፍ ትኩረት እስከ 10000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር እና መቀነስን ማስላት ሲሆን ይህንን አላማ ከግብ ለማድረስ ሦስት ንዑስ ርዕስ ምዕራፎችን ይሸፍናል፡ ፡ እነሱም 10000 ሙሉ ቁጥሮችን መደመር፣እስከ 10000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ እና በመጨረሻም በመደመር እና በመቀነስ ያገኟቸውን ዕውቀቶች በመጠቀም በዕለት ተዕለት የሚያጋጥሟቸውን የመደመር እና መቀነስ የቃላት ፕሮብለሞችን መፍትሄ የሚፈልጉበትን መንገድ ይማራሉ፡፡

ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ማስተማር ውጤቶች

- እስከ 10000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር እና መቀነስ ይረዳሉ።
- እስከ 10000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በመደመር እና መቀነስ ተግባራዊ በማድረግ የቃላት ፕሮብለሞችን ይፈታሉ፡፡

ምዕራፍን ለማስተማር በዋናነት የሚያስፈልጉ የትምህርት መረጃ መሳሪያዎች፡

የመደመር እና የመቀነስ ሰንጠረዦች፣ የቁጥር ቤት ሰንጥረዦች እንዲሁም ተደራራቢ የመደመር ሳጥኖች ይገኙበታል፡፡

## 2.1 እስከ 10000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር

<u>የተመደበው ክ/ጊዜ፡3</u>

### 2.1.1 ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር የብቃቶች

- እስከ 10000 ያሉ የ1000 ብዜቶችን በቃል መደመር
- ባለሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ ሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ጋርመደመር
- ባለሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ ሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ጋርመደመር
- ባለሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ጋርመደመር
- ባለአራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ጋርመደመር

- ባለ ሁለት ሆሄ  ሙሉ ቁጥሮች እንዲደምሩ በቃል እና በፅሑፍ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- ተግባር ሀ ከ1000 የሚያንሱ የ100 ብዜቶችን  በደብተራቸው እንዲሰሩ ማድረግ እና በተግባር ለ የ100 ብዜቶችን በቃላቸው እንዲደምሩ ማድረግ
- ምሳሌ ሀ  በግል እና በጥንድ እንዲሰሩ እና መልሶቻቸውን እንዲያረጋግጡ ማበረታቱ
- ምሳሌ ለ እና ምሳሌ ሐ በተለያየ መንገድ እንዲደምሩ ምላሌዎችን በማሳየተ እና ተጨማሪ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ማድረግ እና ስራዎቻቸውን እንዲያሳዩ ማድረግ
- እስከ 10000 የሚደርሱ ቁጥሮችን በተለያየ መንገድ እንዲደምሩ ማድረግ እና የቤት ስራ ሰርተው መልሶቻቸውን እርማት መስጠት
- ስለ ንዑስ ርዕሱ ማጠቃለያ መስጠት

### 2.1.3 የምዘና ስልቶች እና ዝርዝር ተግባራት

- ከመልመጃዎች የተወሰኑትን  የግል ፣ የቡድን እንዲሁም የቤት ስራ በመስጠት ተማሪዎችን እስከ 10000 የሚደርሱ ቁጥሮችን መደመር እስኪችሉ ድረስ የተለያዩ ተግባራት እና ፕሮብሌሞችን ማሰራት
- ተጨማሪ ጥያቄዎችን መጠየቅ

በዝግታ ለሚረዱ  ተማሪዎች ጥያቄዎች

ሀ. 34+21    ለ. 45+34

በፈጣን ለሚረዱ ተማሪዎች ጥያቄዎች

ሀ.  68+76  ለ. 95+87   ሐ.58×3

### 2.1.4 መልሶች

<u>ተግባር ሀ</u>

1. 0፣100፣ 200፣ 300፣ 400፣ 500፣ 600፣700፣800፣ 900 እና 1000
2. ትንሹ የ100 ብዜት ሙሉ ቁጥር 0 ሲሆን ትልቁ ደግሞ 1000 ነው፡፡

3. ሀ 800 ሐ 600

ለ 1000 መ 1100

**መልምጃ ሀ**

1. ሀ. 7000 ሐ. 9000

ለ. 8000 መ. 10000

2. ሀ. 4481+234 = 4000+400+80+1 +200+30+4

= 4000+600+110+5

= 4000+700+15

= 4715

ለ. 7356+2478 =7000+300+50+6+2000+400+70+8

= 9000+700+120+14

= 9000+800+34 = 9834

ሐ.5750+276 = 5000+700+50+200+70+6

= 5000+900+120+6

= 5000+900+100+20+6

= 5000+1000+20+6

= 6000+20+6 = 6026

መ. 6297+2970 = 6000+200+90+7+2000+900+70

= 8000+1100+160+7

= 8000+1000+100+100+60+7

= 9000+200+60+7 = 9267

3. ሀ. $\begin{array}{r} 686 \\ +\ 18 \\ \hline 704 \end{array}$

ለ. $\begin{array}{r} 8552 \\ +\ 673 \\ \hline 9225 \end{array}$

ሐ. $\begin{array}{r} 1248 \\ +\ 562 \\ \hline 1810 \end{array}$

መ. $\begin{array}{r} 8890 \\ +\ 1256 \\ \hline 10146 \end{array}$

4.

| ሀ | በ | ሀ+በ |
|---|---|---|
| 3400 | 470 | 3870 |
| 4500 | 4530 | 9030 |
| 7800 | 2458 | 10258 |
| 230 | 8800 | 9030 |

## 2.2 እስከ 10000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ

**የተመደበው ክ/ጊዜ:4**

### 2.2.1 ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች

- ባለሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ ሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች መቀነስ
- ባለሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ ሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮ ች መቀነስ
- ባለሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮ ች መቀነስ
- ባለአራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮ ች መቀነስ

### 2.2.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ውይም በአማራጭነት የመማር ማስተማር ዘዴዎች እና ተግባራት

- ባለሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለሦስት ሙሉ ቁጥሮች እንዲቀንሱ ጥያቄዎችን በፅሑፍ መጠየቅ
- ተግባሮችን በቡድን እንዲሰሩ እና በግል እንዲሰሩ ማድረግ
- ምሳሌዎችን በግል እና በጥንድ እንዲሰሩ እና መልሶቻቸውን እንዲያረጋግጡ ማበረታታት
- መቀነስን በብድር እና ያለ ብድር እንዴት እንደሚቀነስ ከሰሩ በኋላ ማስተካከያ በመስጠት ተማሪዎቹን ማበረታታት
- በመቀጠልም ለመቀነስ የተሻለውን አሰራር እንዲመርጡ ማድረግ እና ለተማሪዎች ተጨማሪ ጥያቄዎችን መስጠት፡፡

### 2.2.3 የምዘና ስልቶች እና ዝርዝር ተግባራት

- ከመልመጃዎች የተወሰኑትን የግል ፣ የቡድን እንዲሁም የቤት ስራ በመስጠት ተማሪዎችን እስከ 10000 የሚደርሱ ቁጥሮችን መደመር እስኪችሉ ድረስ የተለያዩ ተግባራት እና መልመጃዎችን ማሰራት
- መልመጃዎቹን ከሰሩ በኋላ ተጨማሪ ጥያቄዎችን የክፍል ስራ በመስጠት ተማሪዎቹን ይመዝኑ፡፡
- ተጨማሪ ምዘናዎች

በዝግታ ለሚረዱ ተማሪዎች

ሀ.65–23 ለ.78–54 ሐ. 82–21

ለፈጣን ተማሪዎች የተለያዩ ጥያቄዎች

ሀ. 38–17 ለ. 67–58 ሐ. 90–78

### 2.2.4 መልሶች

<u>ተግባር ሀ</u>

1. አጠቃላይ የተመሪዎች ብዛት = 32

   የቀሩ ተማሪዎች ብዛት = 4

   በክፍል የሚገኙ ተማሪዎች ብዛት = 32 - 4 = 28 ተማሪዎች

2. አጠቃላይ የአፍሪቃ ሀገራት ብዛት = 55

   አረንጓዴ፣ቢጫ እና ቀይ ቀለማትን የሚጠቀሙ ብዛት = 37

   እነዚህን ቀለማት የማይጠቀሙት የአፍሪቃ ሀገራት ብዛት = 55-37

   = 18

<u>መልመጃ ሀ</u>

1. ሀ. 450 - 42 = 408

   ለ. 568 - 79 = 489

   ሐ. 892 - 678 = 214

2. ሀ.876 -45 = 800+70+6-40-5

= 800+70-40+6-5

= 800+30+6-5

= 800+30+1= 831

ለ. 312-76 = 300+10+2-70-6

= 200+100- 70+12-6

= 200+30+6 = 236

ሐ. 987-296 = 900+80+7-200-90-6

= 900-200+80-90+7-6

= 700+80-90+1

= 600+180-90+1

= 600+90+1

= 691

መ. 650-322 = 600+50-300-20 - 2

= 600-300+50 - 20 - 2

= 300+ 30 - 2

= 328

3. ሀ. $\begin{array}{r} 536 \\ -\ 24 \\ \hline 512 \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 780 \\ -\ 50 \\ \hline 730 \end{array}$

ሐ $\begin{array}{r} 645 \\ -\ 424 \\ \hline 221 \end{array}$ መ. $\begin{array}{r} 989 \\ -\ 435 \\ \hline 554 \end{array}$

4. ሀ $\begin{array}{r} 185 \\ -\ 79 \\ \hline 106 \end{array}$ ለ $\begin{array}{r} 456 \\ -\ 84 \\ \hline 372 \end{array}$ ሐ $\begin{array}{r} 786 \\ -\ 188 \\ \hline 598 \end{array}$ መ $\begin{array}{r} 546 \\ -\ 438 \\ \hline 108 \end{array}$

5.

| ዋና | ተቀናሽ | ልዩነት |
|---|---|---|
| 456 | 78 | 378 |
| 296 | 288 | 8 |
| 720 | 480 | 240 |
| 984 | 164 | 820 |

ተግባር ለ፡

ሀ.በባህር ዳር ስልጠና የወሰዱ = 2400

በሐዋሳ ስልጠና የወሰዱ = 230

ልዩነት ከትልቁ ትንሹን መቀነስ ነው ስለዚህ 2400 - 230 = 2170

ለ .በሐዋሳ ስልጠና የወሰዱ = 230

በጂማ ስልጠና የወሰዱ =2270

ልዩነት ከትልቁ ትንሹን መቀነስ ነው ስለዚህ 2270 - 230 = 2040

መልመጃ ለ

1. ሀ. 6786- 4362 = 6000+700+80+6 - 4000 - 300 - 60 - 2

= (6000 - 4000) + (700 - 300) +(80 -60)+ (6 -2)

= 2000+400+20+4

= 2424

ለ. 8760 - 2084 = 8000+700+60-2000-80-4

= (8000 -2000) + 600 +100 + 60-80 - 4

= 6000+600+(160-80)-4

= 6000 + 600 + 80 - 4

= 6000 + 600 + 70 +10 - 4

= 6000 + 600 + 70 + 6

= 6676

2\. ሀ $\begin{array}{r} 9740 \\ -\ 2370 \\ \hline 7370 \end{array}$ ለ $\begin{array}{r} 5632 \\ -\ 1248 \\ \hline 4384 \end{array}$ ሐ $\begin{array}{r} 7860 \\ -\ 4358 \\ \hline 3502 \end{array}$ መ $\begin{array}{r} 8900 \\ -\ 4300 \\ \hline 4600 \end{array}$

## 2.3 ሙሉ ቁጥሮችን መደመር እና መቀነስ የያዙ የቃላት ፕሮብሌሞችን መፍታት

**የተመደበው ክ/ጊዜ:3**

### 2.3.1 ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች

- ሙሉ ቁጥሮችን በመጠቀም ተግባራዊ ፕሮብሌሞችን መፍታት

### 2.3.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ውይም በአማራጭነት የመማር ማስተማር ዘዴዎች እና ተግባራት

- ተማሪዎችን የማነቃቃት የክፍል ስራዎችን መስጠት
- ተማሪዎች እስከ 10000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር እና መቀነስ በመጠቀም ተግባራዊ ፕሮብሌሞችንእንዲሰሩ ማገዝ
- ተማሪዎች ጥያቄ እንዲጠይቁ፣ሐሳባቸውን እንዲያንፀባርቁ፣እርስ በርስ እንዲነጋገሩና የማጠቃለያ ሐሳብ እንዲሠጡ መፍቀድ

2.3.3 የምዘና ስልቶች እና ዝርዝር ተግባራት

- ስለ ቃላት ጥያቄዎች አፈታት ገለፃ ሰጥቶ ተጨማሪ ምሳሌዎችን መስጠት
- ከመልመጃዎች የተወሰኑትን  የግል ፣የቡድን እንዲሁም የቤት ስራ በመስጠት ተማሪዎችን እስከ 10000 የሚደርሱ ቁጥሮችን የመደመር እና የመቀነስ ተግባራዊ ፕሮብሌሞችን እስኪችሉ ድረስ የተለያዩ ተግባራት እና መልመጃዎችን ማሰራት፣ መከታተል
- በመስጠት ተማሪዎቹን መመዘን
- የወረቀት ሙከራዎችን መስጠት
- ተጨማሪ ምዘናዎች

በዝግታ ለሚረዱ ተማሪዎች

ሀ.የ3ኛ ክፍል ተማሪዎች 400ቢሆኑ እና የ4ኛ ክፍል ተማሪዎች

ደግሞ 380 ቢሆሁ፤አጠቃላይ የ3ኛ እና 4ኛ ክፍል ተማሪዎች ስንት ናቸው?

ለፈጣን ተማሪዎች የተለያዩ ጥያቄዎች

ሀ.የሂለን አባት እድሜ 30 አመት እና የሂለን እድሜ 9 አመት ቢሆን የሂለን አባት እና የሂለን የእድሜ ልዩነት ስንት ነው?

## 2.3.4 መልሶች

### መልመጃ ሀ

1. ዋና = ተቀናሽ + ልዩነት

ሀ. $\begin{array}{r} 678 \\ -\ 560 \\ \hline 118 \end{array}$ ማረጋገጫ 118+560=678

ለ. $\begin{array}{r} 1240 \\ -\ 450 \\ \hline 790 \end{array}$ ማረጋገጫ 790+450 =1240

ሐ . $\begin{array}{r} 3460 \\ +\ 2400 \\ \hline 5860 \end{array}$ ማረጋገጫ 5860 - 2400 = 3460

መ. $\begin{array}{r} 6890 \\ +\ 234 \\ \hline 7124 \end{array}$ ማረጋገጫ $7124 - 234 = 6890$

2. አጠቃላይ የተመረመሩ ሰዎች = 6803

በኮሮና ቫይረስ የተያዙ ሰዎች ብዛት= 467

በኮሮና ቫይረስ ያልተያዙ ሰዎች ብዛት = 6803-467

= 6336

3. የሒሳብ መፅሐፍት ብዛት = 1500

የአማርኛ መፅሐፍት ብዛት= 2000

የእንግሊዘኛ መፅሐፍት ብዛት = 800

አጠቃላይ የመፅሀፍት ብዛት = 1500+2000+800 =4300 4.

የብርቱካን ችግኞች ብዛት = 600

የአቮካዶ ችግኞች ብዛት = 3400

በአጠቃላይ የተተከሉ ችግኞች ብዛት = 3400+600 = 4000

5.አጠቃላይ የተገኙ ጎብኝዎች=9000

የሀገር ባህል ልብሶች የለበሱ =3200

የሀገር ባህል ልብስ ያልለበሱ ጎብኝዎች ብዛት = 9000 - 3200 = 5800

## ምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ መልመጃ

1. ለ. 6222

2. ሀ. 5500

3. መ. 347

4. ሀ. 810

5. ሀ. $\begin{array}{r} 30 \\ +\ 521 \\ \hline 551 \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 7430 \\ +\ 50 \\ \hline 7480 \end{array}$ ሐ. $\begin{array}{r} 2300 \\ -\ 500 \\ \hline 1800 \end{array}$

   መ . $\begin{array}{r} 6721 \\ -\ 5280 \\ \hline 1441 \end{array}$ ሠ. $\begin{array}{r} 4721 \\ +\ 6580 \\ \hline 11301 \end{array}$

6.

| ዋና | ተቀናሽ | ልዩነት |
|---|---|---|
| 5912 | 5678 | 234 |
| 9800 | 9350 | 450 |
| 6700 | 1200 | 5500 |
| 7200 | 6540 | 660 |
| 6892 | 3004 | 3888 |

7. የሁለት ሙሉ ቁጥሮች ልዩነት ለማግኘት ከትልቁ ትንሹን መቀነስ ነው፡፡

8. $\begin{array}{r} 168 \\ -\ 142 \\ \hline 26 \end{array}$

9. ትልቁ ባለሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥር 999 ነው፡፡

   ትንሽ ባለሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥር 100 ነው፡፡

   ልዩነቱ $999 - 100 = 899$

# ምዕራፍ ሦስት

## እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ማባዛት

## መግቢያ

የዚህ ምዕራፍ ዋና ትኩረት እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት ሲሆን ይህንን አላማ ከግብ ለማድረስ ሶስት ንዑስ ምዕራፎች ይኖሩታል። እነዚህም የ100 ብዜት ሙሉ ቁጥሮች በባለ አንድ ሆሄያት ማባዛት፣የማባዛት ውጤታቸው ከ1000 ያነሱ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ማባዛት እና እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛትን መሰረት ያደረጉ የቃላት ፕሮብሌሞችን  መፍታት ይማራሉ።

ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ማስተማር ውጤቶች

- እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ያባዛሉ ፣የ100 ብዜቶችንም ይገነዘባሉ።
- የ10 እና የ100 ብዜቶችን በባለ አንድ ሆሄ ያባዛሉ::
- እስከ 1000 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች ማባዛትን ተግባራዊ ያደረገ መልመጃወችን ይፈታሉ ።

ምዕራፉን ለማስተማር በዋናነት የሚያስፈልጉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

የ100 ብዜት በባለ አንድ ሆሄ የያዙ ሰንጠረዦች፣ የማባዛት ሰንጠረዦች የሚያሳዩ ቻርቶች    እንዲሁም የማባዛት ሰንጠረዥ ይገኙበታል።

### 3.1 የ10 እና የ100 ብዜት ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥረ ማባዛት የተመደበው ክ/ጊዜ :7

#### 3.1.1 ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች

የ10 እና የ100 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማባዛት

#### 3.1.2 ንዑስ ርዕሱን ለማሰተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማር ማስተማር ዘዴና ተግባራ

- እስከ 1000 ያሉ የ10 እና የ100 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮችን በመከለስ የእለቱን ት/ት መጀመር

- የእለቱን ትምህርት አስተዋዉቆ የተግባር ሀ ጥያቄወችን በግል እንዲሰሩ ማድረግና ወደ ማጠቃለያ ሊያደርሳቸው የሚችሉ ሌሎች የቡድን ጥያቄዎችን ሰጥቶ እንዲወያዩባቸውና እንዲሰሯቸው እና ለደረሱባቸው ማጠቃለያ ተጨማሪ ማብራሪያ መስጠት
- በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ብዜት እንዲያስታውሱ ማበረታታት
- የማባዛት ስልቶችን በደንብ እንዲገነዘቡ ማድረግ እና ተደጋጋሚ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ማድረግ

### 3.1.3 የምዘና ስልቶችና ዝርዝር ተግባራት

- ተማሪዎች እስከ 1000 ያሉ የ10 እና የ100 ብዜቶችን በቃላቸው እንዲያባዙ ማድረግ
- መልመጃ ሀ ጥያቄ ውስጥ የተወሰኑትን በክፍልና ቀሪዎቹን በቤት ስራ መልክ መሰጠት
- መልመጃ ሀን መሰረት ያደረጉ ተጨማሪ ጥያቄዎችን መስጠትና እንዲሰሩ ማድረግ መልሳቸውንም ማረጋገጥ
- የወረቀት ሙከራ መስጠት
- ተጨማሪ ምዘናዎች

በዝግታ ለሚረዱ ተማሪዎች

ሀ. $2\times400$ ለ $5\times100$

በፍጥነት ለሚረዱ ተማሪዎች

ሀ. $5\times 2500$ ለ. $15\times300$

### 3.1.4መልሶች

ተግባር ሀ

1. በዜሮ እና በ1000 መካከል የሚገኙ የ100 ብዜቶች በቅደም ተከተል
   100፣200፣300፣400፣500፣600፣700፣800 እና 900 ናቸው።
2. ሀ፣ለ፣መ እና ሠ የአስር ብዜቶች ሲሆኑ ሐ ደግሞ የአስር ብዜት አይደለም
3. ሀ.የ50 የ10 ብዜት 500 የመቶ ብዜትደግሞ 5000 ነው::
   ለ.የ34 የ10 ብዜት 340 የመቶ ብዜትደግሞ 3400 ነው::
   ሐ. 49 የ10 ብዜት 490 የመቶ ብዜትደግሞ 4900 ነው::
   መ.58 የ10 ብዜት 580 የመቶ ብዜትደግሞ 5800 ነው::

መልመጃ ሀ

1. ሀ. 400 ለ. 900 ሐ. 600
   መ. 1000 ሠ. 800 ረ. 2000 ሸ. 0 ቀ. 2400
2. ሀ. የ23 የ10 ብዜት 230 የመቶ ብዜትደግሞ 2300 ነው::
   ለ. የ120 የ10 ብዜት 1200 የመቶ ብዜትደግሞ 12000 ነው::
   ሐ. የ25 የ10 ብዜት 250 የመቶ ብዜትደግሞ 2500 ነው::
   መ. የ10 የ10 ብዜት100 የመቶ ብዜትደግሞ 1000 ነው::

## 3.2 የማባዛት ውጤታቸው ከ1000 ያነሱ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ማባዛት
የተመደበ ክ/ጊዜ :12

### 3.2.1 ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃት

የማባዛት ውጤታቸው ከ1000 ያነሱ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮች ማባዛት

### 3.2.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የመማር ማስተማር ዘዴወች እና ተግባራት

- በቡድን መስራት
- ተግባራት፡ የቡድን እና የግል ስራ

1.ባለሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ያለአለኝታ በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማባዛት

2.ባለሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን በአለኝታ በባለአነድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማባዛት

3.ባለሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ያለ አለኝታ በባለ አንድ ሆሄ ሙሉቁጥር ማባዛት

4.ባለ ሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን በአለኝታ በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማባዛት እንዲሰሩ ማድረግ እና ወደ ማጠቃለያ የሚያደርሱ ተጨማሪ ጥያዌዎችን እንዲወያዩባቸው እና እንዲሰሩ ማድረግ።

### 3.2.3 ምዘና ስልቶችና የዝርዝር ተግባራት

- ከመልመጃ ለ ጥያቄዎች የተወሰኑትን መስራትና የክፍል ስራ ተጨማሪ ጥያቄዎችን መስጠት
- የተወሰኑ ተማሪዎችን ወደ ጥቁር ሰሌዳው በመጋበዝ እንደ

  115×2 , 23×3 , 343×4, ያሉ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ማድረግና መልሶቻቸውን እንዲያረጋግጡ ማድረግ ።
- የወረቀጥ ሙከራ መስጠት

ተጨማሪ ምዘናዎች

በዝግታ ለሚረዱ ተማሪዎች ጥያቄዎች ሀ. 121×2

ለ. 213×2

በፈጣን ለሚረዱ ተማሪዎች የሚሆን ሀ. 1128×2

ለ . 345×5

ሐ. 305×4

### 3.2.4 መልሶች

<u>ተግባር ለ</u>

ሀ. 212×4 = 848 ለ. 43×8 =344

ሐ.355× 2=710 መ.64×3= 192

ሠ. 8×49= 392 ረ. 10×51=510

መልመጃ ለ

1. ሀ.48 ለ. 55 ሐ.64

   መ.78 ሠ. 93 ረ. 0

2. 100x6=600
3. ለ

መልመጃ ሐ

ሀ. 710 ለ. 494 ሐ. 432

መ. 672 ሠ. 918 ረ. 5456

## 3.3 እስከ1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት መሰረት ያደረጉ የቃላት ፕሮብለሞችን የተመደበ ክ/ጊዜ :8

### 3.3.1 ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማረ ብቃት

- ቀላል የማባዛት የቃላት ፕሮብሌሞችን መስራት

### 3.3.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማር ማስተማር ዘዴና ተግባር

- እስ 1000 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች ማባዛትን ተግባራዊ የሚሆንባቸው የቃላት ፕሮብሌሞችንት እንዲስሩ መርዳት
- በቡድን ጥያቄዎችን እንዲሰሩ መርዳት
- ተግባራት፡ በቡድን እና በግል ሆነው ጥያቄዎችን እንዲሰሩ እና የቃላት ፕሮብሌሞችን መስራት እንዲችሉ ማድረግ
- የተግባር ሐ ጥያቄዎችን በቡድን እንዲሰሩ ማድረግና ሌሎች ጥያቄዎችን ሰጥቶ እንዲወያዩባቸውና እንዲሰሯቸው ማድረግና ለደረሱባቸው ማጠቃለያና ተጨማሪ ማብራሪያ መስጠት

### 3.3.3 የምዘና ስልቶችና ዝርዝር ተግባራት

- እስ 1000 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች ማባዛትን ተግባራዊ የሚሆንባቸው የቃላት ፕሮብሌሞችንት እንዲፈቱ መጠየቅ
- መልከታ፣የወረቀት ሙከራ መሰጠት

- ከመልመጃ ረ 1ኛውንና 2ኛውን ጥያቄ የክፍል ስራ 3ኛውን ጥያቄ የቤት ስራ መስጠት
- ተጨማሪ ምዘናዎች

**በዝግታ ለሚረዱ ተማሪዎች ጥያቄዎች ፡**

ሀ.4ዛፎች እያንዳንዳቸው ላይ 12 ወፎች ቢኖሩ፣በአጠቃላይ የወፎች ብዛት ስንት ነው?

ለ.እያንዳንዳቸው የክፍሉ ተማሪዎች 3 ብር ቢያዋጡ በአጠቃላይ ምን ያክል ብር ይሰበስባሉ?

**ለፈጣን ተማሪዎች የሚሆኑ ጥያቄዎች**

ሀ. በአንድ ትምህርት ቤት ውሰጥ ከሚማሩ 538 ተማሪዎች ውሰጥ 500 ተማሪዎች ለበጎ አድራጎት እያንዳንዳችው 8 ብር ቢያዋጡ ፣አጠቃላይ ምን ያክል ገንዘብ ይሰበሰባል?

### 3.3.4 መልሶች

**ተግባር መ**

1. 35×8 = 280 ብር
2. 232×4 = 928 ብር
3. 5 × የተማሪዎች ብዛት

**መልመጃ መ**

1. 32 ፊኛዎች
2. 204 ብር
3. 126 ተጫዋቾች

**የማጠቃለያ መልመጃ ጥያቄዎች መልስ**

1. ሐ
2. ለ
3. ሀ. 393 ለ. 884 ሐ. 2032 መ. 2466
4. 60
5. 3400 ሜትር

ዋቢ መጽሐፍት

- New. Enjoing mathematics .work book with mental maths 3 paper back-1 January 2017
- Every day mathematics Grade 3, student maths Jornal- 2paper back, student Edition , 16 may 2006
- Jica national mathematics text book grade 3, 2019
- Vikas golden mathematics book -4
- Exel basic skill work books — mathematics , 30th ,november 2004
- Maths on the Go book 1 , 15th november 2001.
- Maths- only- maths. com

# የ3ኛ ክፍል ሒሳብ መርሃ ትምህርት

## ምዕራፍ 1 ፡- እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችና ቅደም ተከተላቸዉ(23 ክ/ጊዜያት)

### የመማር ዉጤቶች፣ከዘህ ምዕራፍ ት/ት በኋላ ተማሪዎች፣

- እስከ 10,000 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች ላይ አራቱን መሰረታዊ የሒሳብ ስሌቶቸን ያሰላሉ፡፡
- እስከ 10,000 ባሉ ሙሉ ቁጥሮችን በመገንዘብ ማወዳደር በቅደምተከተል ይጽፋሉ፡፡
- እሰከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በእለት ተእለት ህይወታቸዉ ዉስጥ ይተገብራሉ፡፡

| የመማር ብቃቶች | የትምህርት ይዘቶች | የመማር ማስተማር ስልቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • መቁጠሪያ ቁጥሮችና ሙሉ ቁጥሮች ያላቸዉ ዝምድና<br>• በ አስር በአስር ቡድን በመመደብ የአቆጣጠር ጽንሰ ሃሳብን ማዳበርሩ<br>• የቤት ዋጋ መገንዘብ<br>• እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደርና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ | • 1.1 በ100 እና በ 1000 መቁጠር (2 ክ/ጊዜያት)<br>• 1.2 እሰከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች የቤት ዋጋ (7 ክ/ ጊዜያት)<br>• 1.3 አስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደር (4ክ/ጊዜያት)<br>• 1.4 አስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ቅደም ተከተል (4ክ/ጊዜያት)<br>• 1.5 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ10፤ በ 100 እና በ 1000 ማጠጋጋት (6 ክ/ጊዜያት) | • እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ተግባራዊ ጥቅማቸዉን በመግለጽ ት/ቱን መጀመር<br>• ተማሪዎችን በ አስር በአስር ቡድን በመመደብ የአቆጣጠር ጽንሰ ሃሳብን እንዲያዳብሩ ማገዝ<br>• ሁለት አሃዝ ያለቸዉን ቁጥሮችን አንዱ የአስር ቤት እና ሌላዉ ተጨማሪ የሚለዉን ፅንሳ ሀሳብ እንድያሳድጉ ተማሪዎችን ማገዝ<br>• እስከ 10,000 ያሉ የ100 አና የ 1000 ብዜቶችን እንድ ፈልጉ ተማሪዎችን በቡድን ማደረጀት፣ አርስ በርስ እንድናጋገሩ መርዳት<br>• ተማሪዎች ጥያቄ እንዲጠይቁ፣ ሐሳባቸዉን እንድያንፀባርቁ፤ እርስ በርስ እንዲነገጋሩና የማጠቃለያ ሐሳብ እንዲሠጡ መፍቀድ<br>• እስከ 10,000 ባሉ ሙሉ ቁጠሮች ተግባራዊ ፐሮብሌሞችን እንድሰሩ ማገዝ | • እስከ 100 ያሉ የ10 ብዜቶችን በቃላቸዉእንድነገሩ መጠየቅ<br>• ሙሉ ቁጥሮችን እንደያሰሉ መጠየቅ<br>• የ100 ብዜቶችን በመዘርዘር በቃላቸዉ እንዲቆጥሩ መጠየቅ<br>• እስከ 10,000 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች ተግባዊ ፐሮብሌሞችን እንድሰሩ መጠየቅ<br>• ምልከታ፣የወረቀት ሙከራ መስጠት<br>• የተማሪዎች የመማር ዉጤት እንድሻሻል ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ መስጠት |

## ምዕራፍ 2፡ እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመርና መቀነስ (10 ክ/ጊዜያት)

### የመማር ማስተማር ዉጤቶች፣፣ከዘህ ምዕራፍ ት/ት በኋላ ተማሪዎች፣

- እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመርና መቀነስ ይረዳሉ
- እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በመደመርና መቀነስ ተግባራዊ ፕሮብሌሞችን ይፈታሉ

| የመማር ብቃቶች | የትምህርት ይዘቶች | የመማር ማስተማር ስልቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • እስከ 1,000 ያሉ ቁጠሮችን መደመርና መቀነስ<br><br>ሙሉ ቁጠሮችን በመጠቀም ተግባራዊ ፕሮብሌሞችን መፍታት | 2.1 እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር (3ክ/ጊዜ)<br><br>2.2 እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ (4ክ/ክ/ጊዜ)<br><br>2.3 ሙሉ ቁጠሮችን መደመር እና መቀነስ የያዙ የቃላት ፕሮበሌሞች<br><br>(4ክ/ጊዜ) | • እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በመከለስ እና ተግባራዊ ጥቅማቸውን በመናገር የእለቱን ትምህርት መጀመር<br>• ተማሪዎችን ለማነቃቃት የክፍል ስራ መስጠት ለምሳሌ.ሀ.340+123 ለ.340-123<br>• ተማሪዎች ሙሉ ቁጥርን በ10 ቤት እንድመድቡና በአንድ ቤት ድምር እንዲያስቀምጡት እገዛ ማድረግ<br>ምሳሌ፤ 2+9=1+1+9=1+10=11<br>• ተማሪዎች እስከ 1,000 ያሉ ሙሉቁጥሮችን እንድደምሩና እንድቀንሱ በቡድን እንድወያዩ ፤ እርስ በርሰ እንድናጋገሩ ማገዝ<br><br>• ተማሪዎች እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጠሮችን መደመር እና መቀነስ በመጠቀም ተግባራዊ ፕሮብሌሞችን እንድሰሩ መምራት<br>• ተማሪዎች ጥያቄ እንዲጠይቁ፣ ሐሳባቸዉን እንድያንፀባርቁ፤ እርስ በርስ እንዱነገጋሩና የማጠቃለያ ሐሳብ እንዲሠጡ መፍቀድ | • ተማሪዎች እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቃላቸዉ እንድደምሩ መጠየቅ<br><br>• እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን እንድደምሩና እንዲቀንሱ መጠየቅ<br>• እስከ 10,000 ሙሉ ቁጠሮችን በመጠቀም የዕለት ተዕለት ተግባራዊ ፕሮብሌሞችን እንድሰሩ ተማሪዎችን መጠየቅ<br>• ተማሪዎች የመማር ዉጤታቸዉ እንዲሻሻል ግገንቢየሆነ ግብረ መልስ መስጠት<br>• ምልከታ ማድረግ ወይም የወረቀት ሙከራ መስጠት |

## ምዕራፍ 3፣ እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት (19 ክ/ጊዜያት)

### የመማር ማስተማር ዉጤቶች፣ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኂላ፣

- እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ያባዘሉ፣የ100 ብዜቶችንም ይገነዘባሉ፡፡
- እስከ 1,,000 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች ማባዛትን ተግባራዊ ያደረገ መልመጃዎችን ይፈታሉ፡፡

| የመማር ብቃቶች | የትምህርት ይዘቶች | የመማር ማስተማር ስነዘዴዎች | ምዘና ስልቶች |
|---|---|---|---|
| • የ10 እና የ 100 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁትሮችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁትር ማባዛት<br>• የማባዛት ውጤታቸው ከ1000 ያነሱ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮች ማባዛት<br>• እስከ 1000 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች ማባዛት የያዙ የቃላት ፕሬብሌሞችን መፍታት<br>• የአስር ብዜቶች በአስር የቤተሰብ አባላት ለይ | 3.1 የ 10 እና የ 100 ብዜቶችን በባለ 1 ሆሄያት መባዛት ( 5 ክ/ጊዜያት)<br><br>3.2 የማባዛት ዉጤታቸዉ ከ1000 የነሱሙሉ ቁጥሮችን በበላ አንድ ሆሄ ማባዘት (12 ክ/ጊዜያት)<br><br>3.3 እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛትን መሰረት ያደረጉ የቃለት መልመጃዎች (2ክ/ጊዜያት) | • እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በመከለስ የእለቱን ት/ት መጀመር<br>• የክፍል ስራ በመስጠት ተማሪዎች እንደ<br>10× 5 ያሉ ጥያቄዎችን እንድሰሩ ማናሳሳትና መከታታል<br>• ተማሪዎች የማብዛት ውጤታቸው ከ100 ያልበለጡ ሙሉ ቁጥሮችን የ100 ብዜቶችን በባለ 1 ሆሄ ማብዛትና ሙሉ ቁጥርን በባለ አንድ ሆሄ ማባዛት መሃከል የለዉን ልዩነት እንድለዩ መርዳት<br>• ተማሪዎች የሚከተሉትን የማባዛት ሒደት እንድገልጹ ማድረግ<br>ምሳሌ 786 = 7 × 100 + 8 × 10 + 6 × 1<br>• ተማሪዎች ጥያቄ እንድጠይቁ፣ ሐሳባቸዉን እንድያንፀባርቁ እርስ በርስ እንዲነጋገሩና የማጠቃለያ ሐሳብ እንድሠጡ መፍቀድ<br>• አስር መቶመቶ የሚሆኑ ቁራጭ ወረቀቶችን በመሰብሰብ እስከ 1000 የሠሉ ቁጥሮችን እንዲቆጥሩ እገዛ ማድረግ<br>• እስከ 1000 ያሉ ሙሉቁጥሮችን እንዲያባዙና እንዲያካፍሉ በቡድን እንዲወያዩ ማድረግ<br>• እስከ 1000 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች ማባዛት ተግባራዊ የሚሆንባቸው የቃላት መልመጃዎችን እንዲፈቱ መርዳት<br>• እስከ 1000 ባሉ ቁጥሮች ማባዛትን የያዙ የቃላት መልመጃዎች መፍታት | • ተማሪዎችን እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁትሮችን በቃላቸው እንዲያባዙ መጠየቅ<br>• ተማሪዎች እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁተጥሮች በባለ አንድ ሆሄ እንዲያባዙ እና እንዲያካፍሉ ጥያቄ መጠየቅ<br>• ተማሪዎች እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮች በቀሪ እና ያለ ቀሪ እንዲካፍሉጥያቄ መጠየቅ<br>• ተማሪዎች የመማር ዉጤታቸዉ እንድሻሻል ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ መስጠት<br>• እስከ 1000 ያሉ ተግባረዊ የሚሆነባቸዉን የቃላት ፕሮብሌሞችን እንዲፈቱ መጠየቅ<br>• ምልከታ ፣ የወረቀት ሙከራ መስጠት |

## ምዕራፍ 4፣እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማካፈል (23 ክ/ጊዜያት)

### የመማር ማስተማር ዉጤቶች፣ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኂላ፣

- እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች በ 1,2,3,4,5,6,7,8,9 እና 10 በቀሪና ያለ ቀሪ ማካፋልን ይረዳሉ።
- እስከ 100 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች ማካፈልን ተግባራዊ ያደረገ ፕሮብሌሞችን ይፈታሉ።

| የመማር ብቃቶች | የትምህርት ይዘቶች | የመማር ማስተማር ስነዘዴዎች | የምዘና ስልቶች |
|---|---|---|---|
| • እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በሁለት ያለ ቀሪ ማካፈል<br>• እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በሁለት ፣ 10 እና በአንድ ማካፈል<br>• እስከ መቶ ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን 3,4,5,6,7,8,9 ማካፈል<br>• የ10 ብዜት የሆነ ደሞዝን በ10 የቤተሰብ አባላት ማካፈልን የያዘ የቃላት መልመጃዎችን መፍታት | 4.1አኩል ክፍፍልንና ማካፈልን በተደጋጋሚ መቀነስ (2 ክ/ጊዜ)<br><br>4.2 እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ 2 ያለ ቀሪ ማከፋል (3 ክ/ጊዜ)<br><br>4.3 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ 2 እና በ 10 ማከፈል ( 4 ክ/ጊዜ)<br><br>4.4 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮቾችን በ 1 ማካፈል (2 ክ/ጊዜ)<br><br>4.5 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን 3፣4፣4፣6፣7 8እና 9 በቀሪ እና ያለ ቀሪ ማከፈል (8 ክ/ጊዜ)<br><br>4.6 እስከ 100 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች ማካፈልን የያዘ የቃላት ፐሮብሌሞችን መፍታት ( 4 ክ/ ጊዜ) | • ተማሪዎች እስከ 100 ያሉ የ 10 ብዜቶችን በባለ አንድ ሆሄ ቁጥር እና በ 10 ማከፈል እንድችሉ መርዳት<br>• ተማሪዎች እስከ መቶ ባሉ ሙሉ ቁጥሮች ማካፈልን የያዘ ተግባራዊ የቃላት ፕሮብሌም እንዲሰሩ ማዝ<br><br>• ማከፈልን መሰረት ያደረገ እስከ 100 ባሉ ሙሉ ቁትሮችን በመጠቀም ተግባራዊ መልመጃዎችን እንድሰሩ ማገዝ | • እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቀጥሮች በቃለቸዉ እንዲያካፍሉ መጠየቅ<br>• ተማሪዎች እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ እንደያካፍሉ ማካፈል መጠየቅ<br>• ማከፈልን መሰረት ያደረገ እስከ 100 ባሉ ሙሉ ቁጥሮችን በመጠቀም ተግባራዊ ፕሮብሌሞችን እንድሰሩ ማመጠየቅ<br>• ተማሪዎች የመማር ዉጤታቸዉ እንድሻሻል ግልፅ የሆነ ግብረ መልስ መስጠት<br>• የቃል ፣ የወረቀት ሙከራ መስጠት<br>• እስከ 100 ያሉ ሙሉቁጥሮችን በባለ እንድ ሆሄ በቀሪ እና ያለቀሪ እንዲያካፍሉ መጠየቅ |

## ምዕራፍ 5፣ ክፍልፋዮች (23 ክ/ጊዜያት)

### የመማር ማስተማር ዉጤቶች፣ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፣

- ክፍልፋዮች የሙሉ ቁጥር ክፍሎች እንድሆኑ ይረዳሉ፡፡
- በክፍልፋየች ተግባራዊ የሚሆኑ መልመጃዎችን ይሰራሉ፡፡

| የመማር ብቃቶች | የትምህርት ይዘቶች | የመማር ማስተማር **ስልቶች** | የምዘና ስልቶች |
|---|---|---|---|
| • ግማሽ፣የሲሶ እና የሩብ ምንነትን መለየት፣ማወዳደር<br><br>• ከ1/2-1/10 ያሉ አሃዳዊ ክፍልፋዮችን በቁጥር መስመር ላይ ማንበብ፣ መጻፍ<br>• የክፍልፋዮችን ሃሳቦች አረዳድ ለማሳድግ የአንድ ሙሉነገር ክፍል፣የስብስቦች አካል፣ በቁጥር መሰመር ላይ ማማልከት፣ እና የሙሉቁጥሮች ተካፋይነትን መጠቀም<br>• አቻ ክፍልፋዮችን ተመሳሳይ በሆኑ ቁጥሮች በማብዛት ወይም በማቃለል መግለጽ<br>• የተለመዱ ክፍልፋዮችን በመጠቀም አቻ ክፍልፋዮችን መረዳት፣ መተንተን<br>ክፍልፋዮችን መግለጽ<br>• ከእለት ተእለት ህወታቸዉ ጋር የተያያዙ ክፍልፋዮችን እንደ ግማሽ፣ ሲሶ እና ሩብ ፕሮብሌሞችን በተለመደ ቅርጽ(ጎነአራት፣ ክብ…)በመጠቀም መስራት | 5.1 ግማሽ፣ሲሶና ሩብ<br>(6 ክ/ጊዤያት)<br><br><br>5.2 ከ ½ እስካ 1/10 ያሉ አሃዳዊ ክፍልፋች<br>(8 ክ /ግዜያት)<br><br><br>5.3 ግማሽ እና ሩብ<br>4ክ/ ጊዜያት)<br><br>5.4 ክፍልፋዮችን መግለጽ<br>(5 ክ/ጊዜያት) | • ክፍልፋዮች የሙሉ ቁጥር ክፍሎች እንድሆኑ መግለጽ<br>• ተማሪዎች ክፍልፋዮችን ሞዴል በመጠቀም ግመሽ፣ ሩብ፣ ሲሶ አንድ አረተኛ፣… እንድያብራሩ ማገዝ<br>• ተማሪዎች ከሞዴል ለይ ግማሹን በመቀባት የተቀባዉን ከሙሉ ሞዴል ጋር በማነፃፀር እንድገልፁ እና አቻ ክፍልፋዮችን እንዲፈልጉ ማገዝ<br>• ተማሪዎች በቡድን በመሆን በመወያየት እና በመረዳዳት አቻ ክፍልፋዮች እንዲፈልጉ ማድረግ<br>• ታመሪዎች ጥያቄ እንዲጠይቁ፣ እንዲገምቱ፣እንዲያጠቃልሉ እና ዉጤታቸዉን እንዲያጸባርቁ እና እንዲያዛምዱ መድረግ<br>• በክፍልፋዮች ተግባራዊ የሚሆኑ መልመጃዎችን እንዲሰሩ ማገዝ<br> | • ተማሪዎች ክፍልፋዮችን እንድያነቡና እንድፅፉ መጠየቅ<br>• በቁጥር መስመር ለይ ክፍልፋዮችን እንዲያመለክቱ መጠየቅ<br>• ተማሪዎች አቻ ክፍልዮችን እንዲያወዳድሩና እንዲለዩ መጠየቅ<br><br>• በክፍልፋየች ተግባራዊ የሚሆኑ ፕሮብሌሞችን እንዲሰሩ መጠየቅ<br><br>• ተማሪዎች የመማር ዉጤታቸዉ እንድሻሻል ግልፅ የሆነ ግብረ መልስ መስጠት<br>• ምልከታ ፣ የወረቀት ሙከራ መስጠት |

## ምዕራፍ 6፣ንድፎች (9 ክ/ጊዜያት)

### የመማር ማስተማር ዉጤቶች፣ ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፣

- ቀጣይነት ያላቸዉን ንድፎች ይረዳሉ፡፡
- ተግባራዊ የንድፍ ፐሮብሌሞችን ይፈታሉ፡፡

| የመማር ብቃቶች | የትምህርት ይዘቶች | የመማር ማስተማር ስልቶች | ምዘና ስልቶች |
|---|---|---|---|
| • እያደገ ያለ ንድፍ መለየት<br><br>• እያደገ ያለ ንድፍ ማስቀጠል<br><br>• የሚደጋገሙና የሚያድጉ ንድፎችን ሩቅ አባለቱን መተንበይ | 6.1 ቀጣይነት ያለቸዉ ንድፎችን መለያት (3 ክ/ጊዜ)<br><br>6.2 እያደገ ያለ ስዕላዊ ንድፍ ማስቀጠል (3 ክ/ጊዜ)<br><br>6.3 ቀጣይነትና ተደጋገሚነት ያላቸዉን የሩቅ አባላት ንድፎችን መተንበይ (3 ክ/ጊዜ) | • በቀጠይነት ያላቸዉን ንድፎች እንዲፈልጉ ምሳሌ በመዉሰድ ለተማሪዎች ማሳየት፣<br>• የሚደግሙና የሚድጉ ንድፎችን ሩቅ አባለቱን መተንበይ እንዲችሉ መረዳት<br><br>• ተማሪዎች በቡድን ሆነዉ እያደገ ያለ ንድፍን እንዲለዩ፣እያደገ ያለ ንድፍን እንዲያስቀጥሉ፣ የሚደግሙና የሚያድጉ ንድፎችን ሩቅ አባላቱን እንዲተነብዩ አርስ በርስ እንድነጋገሩ ማገዝ<br><br>• ቀጣይነት ያላቸዉን ንድፎች በምስል እና በምሳሌ እንድሰሩ ማድረግ፣ ተደጋገሚ ንድፎችን እንድለዩ ማገዝ<br><br>• ሦስት እስከ አራት አባላት ያሉትን ንድፎች በመዉሰድ 100 ወይም 1000 ኛ አባለቱን እንዲሉዩ መደገፍ፣ቀመር እንዲፈልጉ መርዳት<br><br>• ተግባራዊ የንደፍ ፐሮብሌሞችን እንድሰሩ ማበረታታት<br><br>• ተማሪዎች ጥያቄ እንድጠይቁ፣ ሐሳባቸዉን እንድያንፀባርቁ እርስ በርስ እንድነገጋሩነ የማጠቃለያ ሐሳብ እንድሠጡ መፍቀድ | • ቀጣይነት ያላቸዉን ንድፎች እንድለዩ፣ እንድያስቀጥሉ፣ በርቀት ያሉ አባለቱን እንድያሚሉ መጠየቅ<br><br>• ምልከታ ወይም በወረቀት ሙከራ መስጠት<br><br>• ተማሪዎች የመማር ዉጤታቸዉ እንዲሻሻል ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ መስጠት |

## ምዕራፍ 7፣ እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት እና ማካፈል (16 ክ/ጊዜያት)

### የመማር ማስተማር ዉጤቶች፣ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፣

- እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ያባዘሉ፣የ100 ብዜቶችንም ያባዘሉ፡፡
- እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁትሮችን በባላ አንድ ሆሄ ያካፍላሉ
- እስከ 1,,000 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች ማባዛትን ተግባራዊ ያደረገ መልመጃዎችን ይፈታሉ፡፡

| የመማር ብቃቶች | የትምህርት ይዘቶች | የመማር ማስተማር ስነዘዴዎች | ምዘና ስልቶች |
|---|---|---|---|
| • የ10 እና የ 100 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁትሮችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማባዛት<br>• የማባዛት ውጤታቸው ከ1000 ያነሱ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮች ማባዛት<br>• እስከ 10000 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች ማባዛት የያዙ የቃላት ፕሬብሌሞችን መፍታት<br>• የአስር ብዜቶች በአስር የቤተሰብ አባላት ለይ | 7.1 የ 1000 ብዜቶችን በባለ 1 ሆሄያት ሙሉ ቁጥር መባዛት ( 4 ክ/ጊዜያት)<br><br>7.2 የ10 እና የ 100 ብዜት ሙሉ ቁጥሮችን በበላ አንድ ሆሄ ማካፈል (4 ክ/ጊዜያት)<br><br>7.3 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባላ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማባዛት (4ክ/ጊዜያት)<br>7.4 እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባላ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማካፈል (4ክ/ጊዜያት) | • እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በመከለስ የእለቱን ት/ት መጀመር<br>• የክፍል ስራ በመስጠት ተማሪዎች ጥያቄዎችን እንድሰሩ ማናሳሳትና መከታታል<br>• ተማሪዎች የማብዛት ውጤታቸው ከ100 ያልበለጡ ሙሉ ቁጥሮችን የ100 ብዜቶችን በባላ 1 ሆሄ ማብዛትና ሙሉ ቁጥርን በባለ አንድ ሆሄ ማባዛት መሃከል የለዉን ልዩነት እንድለዩ መርዳት<br>• ተማሪዎች የሚከተሉትን የማባዛት ሒደት እንድገልጹ ማድረግ<br>• ተማሪዎች ጥያቄ እንድጠይቁ፣ ሐሳባቸዉን እንድያንፀባርቁ እርስ በርስ እንዲነጋገሩና የማጠቃለያ ሐሳብ እንድሠጡ መፍቀድ<br>• አስር መቶመቶ የሚሆኑ ቁራጭ ወረቀቶችን በመሰብሰብ እስከ 1000 የሠሉ ቁጥሮችን እንዲቆጥሩ እገዛ ማድረግ<br>• እስከ 1000 ያሉ ሙሉቁጥሮችን እንዲያባዙና እንዲያካፍሉ በቡድን እንዲወያዩ ማድረግ<br>• እስከ 1000 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች ማባዛት ተግባራዊ የሚሆንባቸው የቃላት መልመጃዎችን እንዲፈቱ መርዳት<br>• እስከ 10,000 ባሉ ቁጥሮች ማባዛትን የያዙ የቃላት መልመጃዎች መፍታት | • ተማሪዎችን እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁትሮችን በቃላቸው እንዲያባዙ መጠየቅ<br>• ተማሪዎች እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች በባለ አንድ ሆሄ እንዲያባዙ እና እንዲያካፍሉ ጥያቄ መጠየቅ<br>• ተማሪዎች እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮች በቀሪ እና ያለ ቀሪ እንዲካፍሉጥያቄ መጠየቅ<br>• ተማሪዎች የመማር ዉጤታቸዉ እንድሻሻል ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ መስጠት<br>• እስከ 1000 ያሉ ተግባረዊ የሚሆነባቸዉን የቃላት ፕሮብሌሞችን እንዲፈቱ መጠየቅ<br>• ምልከታ ፣ የወረቀት ሙከራ መስጠት |

## ምዕራፍ 8 የመረጃ አያያዝ (11 ክ/ጊዜያት)

### የመማር ማስተማር ዉጤቶች ፣ ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ

- ስዕላዊ ግራፎችን እንዴት እንደሚገልፁ ይረዳሉ ።
- ስዕላዊ ግራፎችን በነባራዊ ህወታቸዉ ላይ ይተገብራሉ።

| የመማር ብቃቶች | የትምህርት ይዘቶች | የመማር ማስተማር ስልቶች | የምዘና ስልቶች |
|---|---|---|---|
| • የፍራፍሬ ምስሎችን በመጠቀም ስዕለዊ ግራፎችን መስራት<br><br>• መረጃን ከስዕላዊ ግራፍ ለይ ያነባሉ ፣በጣም ትልቁ፣ ትንሹን ና የተደጋገመ መረጃ፣ በትልቁና በትንሹ ሙህከል ያለዉን መረጃ ልዩነት መነገር | 8.1 ስዕላዊ ግራፎች (5ክ/ጊዜ)<br><br>8.2 ስዕለዊ ግራፎችን ማንበብና መፃፍ (6 ክ /ጊዜ) | • ስዕለው ግራፎችን ከአካባቢያቸዉ ባለ መረጃ እንዲሰሩ የቡድን ስራ መስጠት<br>• ተማሪዎች ስዕላዊ ግራፎችን ስገልፁ ትንሽ፣ብዙ፣ በጣም ብዙ፣ የሚሉ ቃላትን ተጠቅመዉ ማብራሪያ እንድሰጡ ማድረግ<br>• ተማሪዎች መረጃን ከ ግራፍ እንዲያነቡና እንዲያብራሩ መረዳት<br>• ተማሪዎች በቡድን ሆነዉ እርስ በርስ እንድነጋገሩ ማገዝ<br>• ተማሪዎች ጥያቄ እንድጠይቁ፣ ሐሳባቸዉን እንድያንፀባርቁ እርስ በርስ እንድነገጋሩ የማጠቃለያ ሐሳብ እንዲሠጡ መፍቀድ<br>• ስዕላዊ ግራፎችን በነባራዊ ህወታቸዉ ለይ እንዲተገብሩ መርዳት<br><br>• በኢትዮጽያ በየዕለቱ የኮረና ቭይረስ ስርጭት መጨመር በስዕላዊ ግራፍ እንዲስሉ ማድረግ | • ስዕላዊ ግራፎችን እንዲስሉ ማድረገ<br>• ከስዕላዊ ግራፍ ለይ መረጃ እንዲያነቡ ፣እንዲገልፁ መጠየቅ<br>• መረጃን መሰረት ያደረጉ የቃለት ፕሮብሌሞችን እንድሰሩ ማገዝ<br>• ምልከታ ወይም የወረቀት ሙከራ መስጠት<br><br>• ተማሪዎች የመማር ዉጤታቸዉ እንዲሻሻል ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ መስጠት |

## ምዕራፍ 9፣የጂኦሜትሪ ምስሎች (20 ክ/ጊዜያት)

የመማር ማስተማር ዉጤቶች፣ ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፣

- ምጥጥን መስመር ያላቸዉና የሌላቸዉ ምስሎችን ይረዳሉ፡፡
- የጂኦሜትሪ ምስሎችን በጎናቸዉ ቁጥር መሰረት መለየት ይችላሉ፡፡
- የጂኦሜትሪ ምስሎችን ባህሪያት ይለያሉ፡፡

| የመማር ብቃቶች | የትምህርት ይዘቶች | የመማር ማስተማር ስልቶች | የምዘና ስልቶች |
|---|---|---|---|
| • ማዕዘን ለመረዳት አራት መዕዘን የሆኑ ወረቀቶችን ማንሸራተት፣ ማንፀባራቅ መጠቀም<br><br>• ምጥጥን የሆኑ ና ያልሆኑ ቅርፆችን መለያት<br><br>• የጂኦሜትሪ ምስሎችን በስም መጥራት<br><br>• የጂኦሜትሪ ምስሎችን በህሪያት መገንዘብ | 9.1 ማዕዘን መረዳት የተንሸራታች፣ ግልበጣዎችእና ማንፀባራቅ አተገባባር(5 ክ/ገዜ)<br><br>9.2 ምጥጥን ቅርፅ ያላቸዉ እና የሌላቸዉን መለያት (5 ክ//ግዜ)<br><br>9.3 በጎነቸዉ መሰረትየጂኦሜትሪ ምስሎችን መለያትና መሰያም (5 ክ//ግዜ)<br><br>9.4 የጂኦሜትሪ ቀርፃችን ባህሪያት ማደረጀትና መሰየም (5 ክ//ግዜ) | • ተንሸራታች፣ ግልበጣዎች እና ማንፀባራቅ በማቅረብመዕዘን እንዲገነዘቡ ማድረግ<br>• ወረቀት በመጠቀም ምጥጥንና ምጥጥን ያልሆኑ ምስሎችን እንድለዩ መርዳት<br>• ተማሪዎች በቡዲን ሆነዉ የጂኦሜትሪ ምስሎችን በባህሪያቸዉ እንዲለዩ፣ አረርስ በርስ እንድነጋገሩ ማገዝ<br>• ተማሪዎች ጥያቄ እንድጠይቁ፣ ሐሳባቸዉን እንድያንፀባርቁ እርስ በርስ እንድነገጋሩ የማጠቃለያ ሐሳብ እንድሠጡ መፍቀድ<br>• ጠጣር ምስሎችን በማቅረብ ተማሪዎች መዕዘን፣ጠርዝ እንዲለዩ ማገዝ<br><br><br><br><br>• የጂኦሜትሪ ምስሎችን መሰረት ያደረጉ ተግባራዊ የቃለት መልመጃዎችን እንድሰሩ ማገዝ | • ተንሸራታች፣ ግልበጣዎች እና ማንፀባራቅ በማቅረብ መዕዘን እንዲገነዘቡ መጠያቅ<br>• የጂኦሜትሪ ምስሎችን በባህሪያቸዉ እንድለዩ መጠየቅ<br>• የጂኦሜትሪ ምስሎችን መሰረት ያደረጉ ተግባራዊ የቃለት ፕሮብሌሞችን እንድሰሩ መጠየቅ<br>• ምልከታ እና የወረቀት ሙከራ መስጠት<br>• ተማሪዎች የመማር ውጤታቸዉ እንዲሻሻል ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ መስጠት |

## ምዕራፍ 10 ልኬት ፤ ርዝመት፣ መጠነቁስ እና ይዘት (15ክ/ጊዜያት)

### የመማር ማስተማር ዉጤቶች፣ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፣

- ተማሪዎች ርዝመት፣ መጠነቁስና ይዘትን ይረዳሉ፣ለእያንዳዳቸዉ ትክክለኛ የመለክያ ምድብ ይለያሉ፡፡
- በመሰረታዊ የመለኪያ አሀዶች የመለካት ጥቅሞች ይረዳሉ፣በተለምዶ እና ሜትሪክ ሲስተም ጋር መሰረታዊ የመለኪያ ምድቦች ጋር በደንብ ይተዋወቃቃሉ
- ልኬቶችን በመጠቀም ቀላል የምድብ ቅይይሮችን ይሰራሉ ምሳሌ የልኬት ዘዴዎችን በመጠቀም ከ ሴ.ሜ ወደ ሜ ይለወጣሉ፡፡
- ርዝመት፣መጠነቁስና ይዘትን የያዙ የዕለትተዕለት ፐሮብሌሞችን ይሰራሉ፡፡

| የመማር ብቃቶች | የትምህርት ይዘቶች | የመማር ማስተማር ስልቶች | የምዘና ስልቶች |
|---|---|---|---|
| • የርዘመት መለኪያ ምድቦችን መለየት<br>• ቁሶችን በተለያዩ ርዝመት ምድቦች መለከት<br>• የትናንሽ ቁሶች መጠነ ቁስ መለካት<br>• የቁሶችን ይዘት መለካት በኩባያ ያለ አሸዋ ወይም ዉሃ በመጠቀም መለካት<br>• የመማሪያ ክፍላቸዉን በር፣ መስኮት እና ጠረጴዛ በሜ እና በሳ.ሜ መለካት | 10.1 ርዝመትን ፣በሚሜ፣በሰሜ፣ በሜ እን በኪ.ሜ መለከት (2ክ/ጊዜ)<br>10.2 ተመሳሳይ አሃድ ያለቸዉን ርዝመቶች መደመርና መቀነስ (3ክ/ጊዜ)<br>10.3 መጠነቁስ በሚግ፣ግ፣ክግ፣እና በኩንታል መለካት (3 ክ/ጊዜ)<br>10.4 ተመሳሳይ አሃድ ያላቸዉን መጠነቁስ መደመርና መቀነስ(3ክ/ጊዜ)<br>10.5 ይዘት መሚሊ፣በሊተር እና በጋሎን መለካት(2ክ/ጊዜ)<br>10.6 ተመሳሳይ አሃድ ያለቸዉን ይዘቶች መደመርና መቀነስ (2ክ/ጊዜ) | • የርዝመት፣መጠነቁስ እና የይዘትን መነሻ በማስቀመጥ በተለምዶ የምንጠቀማቸዉን እንደ ክንድ፣ እርምጃ... ወዘተ ጋር እንዲያነፃፅሩ ማብራሪያ እንድሰጡ ማድረግ<br>• በሀላዊ የርዝመት መለክያ ሀአዶዎችን በመጠቀም ርዝመትን እንድለኩ መድረግ<br>• ለእያንዳንዳቸዉ ልኬቶች ሞዴሎችን ማዘጋጀት<br>• የተለያዩ የመለኪያ ምድቦችን ፅንሳ ሀሳብ እንዲያዳብሩ ማድረግ<br>• ከመሰረታዊ የመለኪያ ምድቦች ጋር ዝምድና እንድያደብሩማድረግ<br>• አሰር ባለ 100ሳ.ሜ ርዝመት ያለቸዉ ክሮችን አንድ ላይ በመደመር 1000ሳ.ሜ እንደሚሰጡ ማሳየት<br>• ልኬትን በማስመሪያ ስለኩ ከ ቀኝ መጨረሻ እንዲጀምሩ ማገዝ<br>• ተማሪዎች ጥያቄ እንድጠይቁ፣ ሐሳባቸዉን እንድያንፀባርቁ እርስ በርስ እንድነገጋሩነ የማጠቃለያ ሐሳብ እንድሠጡ መፍቀድ<br>• ወስን መስመሮች ርዝመት ለመለካት ጂኦአልጀብራ መጠቀም<br>• ልኬትን መሰረት የደረጉ ተግባራዊ መልመጃዎችን መግበር ምሳሌ ፣ የክፍላቸዉን በር፣ መስኮት .. እንድለኩ ማገዝ | • ተተማሪዎች በተመሳሳይ ምድብ ያላቸዉን የተለያ ልኬቶችን እንድለዩ መጠየቅ<br>• ልኬትን መሰረት የደረጉ ተግባራዊ መልመጃዎችን መተግበር<br>• የምልከታ ወይም በወረቀት ሙከራ መስጠት<br>• ተማሪዎች የመማር ዉጤታቸዉ እንድሻሻል ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ መስጠት |

## ምዕራፍ 11፡- የኢትየጵያ ገንዘብ

### የተለያዩ የኢትዮጵያ የገንዘብ ኖቶች (13 ክ/ጊዜያት)

**የመማር ማስተማር ዉጤቶች ፣ ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፣**

- ኢትዮጵያ የተለያዩ የገንዘብ ኖቶች እንደሏት ይረዳሉ፡፡
- አንድ የገንዘብ ምንዛሬ ወደ ሌላ የገንዘብ ኖት  እንዴት መለወጥ (መቀየር) እንዳለባቸዉ ይወስናሉ፡፡
- የኢትዮጵያን ገንዘብ በእለት ተእለት ህይወታቸዉ ይጠቀማሉ፡፡

| የመማር ብቃቶች | የትምህርት ይዘቶች | የመማር ማስተማር **ስልቶች** | የምዘና ስልቶች |
|---|---|---|---|
| • ሣንቲሞችን መገንዘብ<br>• የሳንቲሞችን ጥቅም መረዳት፣ መገንዘብ<br>• የሳንቲሞችን ስብስብ ማወዳደር<br>• ለአንድ በተሰጠ የገንዘብ መጠን  ተመሳሳይ የተለያዩ አይነት ሳንቲሞችን መፈለግ<br>• ለአንድ ተሰጠ የገንዘብ መጠን ተመጣጣኝ ሳንቲሞችን መፈለግ<br>• የገንዘብ ምንዛሪ ማድረግ<br>• የገንዘብ ፅንሳ ሀሳብ ያላቸዉን የቃላት መልመጃ መፍታት | 11.1 የገንዘብ ምንዛሪ ምድብ (7 ክ/ጊዜ)<br><br>11.2 የገንዘብፅንስ ሀሳብ ያላቸዉ የቃለትፐሮብሌሞች (6 ክ/ጊዜ) | • የኢትዮጵያ የገንዘብ ኖቶች ያሉበትን ሞዴል ከአንድ ሳንቲም እስከ 200 ብር ድረስ በማቅረብ ተማሪዎች እንድረዱት ማድረግ<br>• ተማሪዎች አንድን የገንዘብ ኖት ወደ ተለያዩ ኖቶች እንድቀይሩ ማገዝ<br>• የገንዘብ ፅንሳ ሀሳብ ያላቸዉን የቃላት ፐሮብሌም መፍታት<br>ምሳሌ አንድ ዳቦ 2 ብር ከ 50 ሳንቲም ከሆነ በ 25 ብር ስንት ዳቦ መግዛት ይቻላል<br>• ተማሪዎች በቡድን ሆነዉአንድ የገንዘብ ምንዛሪ ወደ ሌላ የገንዘብ ኖት  እንዴት መለወጥ እነዳለባቸዉ እርስ በርስ እንድነጋገሩ መርዳት<br>• ተማሪዎች ጥያቄ እንድጠይቁ፣ ሐሳባቸዉን እንድያንፀባርቁ እርስ በርስ እንድነጋሩ የማጠቃለያ ሐሳብ እንዲሠጡ መፍቀድ | • ተማሪዎች የተለያዩ የገንዘብ ኖቶችን  እንድለዩ፣እንድመነዝሩ መጠየቅ<br>• ገንዘብ ፅንሳ ሀሳብ መሰረት ያደረጉ  የቃላት ፐሮብሌሞችን እንድሰሩ ማድረግ<br>• ተማሪዎች የመማር ዉጤታቸዉ እንድሻሻል ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ መስጠት<br>• ምልከታ ወይም በወረቀት ሙከራ መስጠት |

## ምዕራፍ 12 ፡- የኢትዮጵያ ጊዜ (13 ክ/ጊዜያት)

### የመማር ማስተማር ዉጤቶች፣ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፣

- የኢትዮጵያ የጊዜ (የሠዓት) አቆጣጠር ማንበብ ይረዳሉ፡፡
- አንድ የጊዜ ምድብ ወደ ሌላ የጊዜ ምድብ መለወጥ ይችላሉ፡፡
- የኢትየጵያ ግዜን መሰረት ያደረገ ተግባራዊ መልመጃዎችን ይተገብራሉ፡፡

| የመማር ብቃቶች | የትምህርት ይዘቶች | የመማር ማስተማር ስልቶች | የምዘና ስልቶች |
|---|---|---|---|
| • የሰዓትና የደቂቃ አመልካቾችን መለየት<br><br>• ሠዓቶችን ወደ ደቂቃዎች መቀየር<br><br>• አመታትን ወደ ወራት፣ ሳምንታት እና ቀናት መቀየር<br><br>• ግዜን መሰረት ያደረጉ የቃላት መልመጃዎችን መተግበር | 12.1 ሰዓቶችን ማንበብ (3 ክ/ጊዜ)<br><br>12.2 ሰዓትና ደቂቀዎች (4 ክ/ግዜ)<br><br>12.3 ቀናት፣ ሳምንታት፣ ወረትና አመታት (4 ክ/ግዜ)<br><br>12.4 የኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር (2 ክ/ግዜ) | • የሰዓት ሞዴል በማቅረብ ተማሪዎች የሰዓትን የደቂቃ አመልካቶችን እንድለዩ መርዳት<br>• የሰዓት ሞዴል በማቅረብ ተማሪዎች የሰዓትን ወደ ደቂቃ፣ ደቂቃን ወደ ሰዓት እንድቀይሩ መድረግ እና ያለ ሰዓት ሞዴል ቅይይሩን እንድሰሩ ማድረግ<br>• ተማሪዎች በቡድን ሆነዉ ሰዓትን ወደ ደቂቃ፣ ዓመታትን ወደ ወራት፣ሳምንታት እና ወደ ቀናት እንድቀይሩ ማገዝ<br>• የኢትየጵያ የዘመን አቆጣጠር(ከለንደር) ማቅረብ<br>• ግዜን መሰረት ያደረጉ የቃላት ፕሮብሌሞችን እንድሰሩ ማገዝ<br>• ተማሪዎች ጥያቄ እንድጠይቁ፣ ሐሳባቸዉን እንድያንፀባርቁ እርስ በርስ እንድነገጋሩ የማጠቃለያ ሐሳብ እንድሠጡ መፍቀድ | • ተማሪዎች የተለያዩ የእትዮጺያ የግዜ ምድቦችን እንድለዩና እንድቀያይሩ መጠየቅ<br><br>• ግዜን መሰረት ያደረጉ የቃላት ፕሮብሌሞችን እንድሰሩ መጠየቅ<br><br>• ተማሪዎች የመማር ዉጤታቸዉ እንዲሻሻል ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ መስጠት<br><br>• የምልከታ ወይም በወረቀት ሙከራ መስጠት |